

# አባሪ ለ (Appendix B)

# በቀዶ ጥገና የውስጠኛውን የጆሮ ክፍል መተካት እና የመስማት ችሎታ (Cochlear implants and hearing)

*የጆሮ የውሰጥ ክፍሎች*




ሰዎች ድምፅን መስማት የሚችሉት በውስጠኛው የጆሮ ክፍል ውስጥ የሚገኘው ኮክሊያ (cochlea) የሚባለው አካል የድምፁን መልዕክት ተቀብሎ ወደ አእምሮ ሲያስተላልፍ ነው:: ስለዚህ አንድ ሰው በኮክሊያው ላይ ጉዳት ከደረሰበት በደንብ ሊሰማ አይችልም::

ኮክሊያን በቀዶ ጥገና የመተካት ዘዴ መስማት የተሳናቸውን ሕፃናት መስማት እንዲችሉ ለመርዳት የተጀመረ አዲስ ቴክኒዎሎጂ ውጤት ነው:: ይህ ዘዴ እጅግ በጣም ውድ ቢሆንም እንኳ በአሁኑ ጊዜ በብዙ አገሮች በተግባር ላይ እየዋለ ይገኛል::

ሰው ሰራሽ 'ኮክሊያን' ለአንድ ሰው ለመስጠት የራስ ቅሉ በቀዶ ጥገና መከፈት አለበት:: ከዚያም በጣም ትንሽ የሆነ ኮክሊያውን ሊተካ የሚችል 'ኮክሊአር ኢምፕላንት' (cochlear implant) የሚባል መሳሪያ በውስጠኛ ው ጆሮ በስተመጨረሻው ክፍል ውስጥ ይቀበራል::

'ኮክሊያ' (cochlea) በጭንቅላት ውስጥ የሚገኝ ትንሽ የጆሮ ክፍል ነው:: ቅርፁም የቀንድ አውጣን ሽፋን ይመስላል::

**'የኮክሊያ ኢምፐላንት' ክፍሎች**

'የኮክሊያ ኢምፐላንት' ግማሹ ክፍል በጭንቅላት ውስጥ ሲሆን:: ሌሎቹ ክፍሎች ደግሞ በውጪ (በራስ ላይ) ልክ እንደ መስሚያ መርጃ መሳሪያ የሚደረጉ ናቸው::



## *'በኮክሊያ ኢምፕላንት'* ሊጠቀም የሚችል ሰው ማን ነው?

*የ'ኮክሊያ ኢምፕላንት'* የሚደረገው ሙሉ በሙሉ መስማት ለተሳናቸው ሕፃናት ወይም የመስሚያ መርጃ መሳሪያንም ተጠቅመው እንኳ በጣም በትንሹ ብቻ ለሚሰሙ ሕፃናት ብቻ ነው፡፡ በአንዳንድ አገሮች ዕድሜአቸው ገና 6 ወር ለሆናቸው ሕፃናትም 'ኮክሊያ ኢምፕላንት' ሲደረግ፣ በሌሎች አገሮች ደግሞ ዕድሜአቸው ከ 1 እስከ 2 ዓመት ለሆናቸው ይደረጋል፡፡ የኮክሊያ ኢምፕላንት አስቀድሞውኑ ትንሽም ቢሆን የመስማት ችሎታ ላላቸው ሰዎች አይረዳቸውም፡፡

## *የ'ኮክሊያ ኢምፕላንት'* በመስማት ላይ የሚያደርገው ተፅዕኖ

ኮክሊያ ኢምፕላንቶች መስማት መሳንን አይፈውሱም፡፡ በውጪ የሚገኙት የመሳሪያው ድምፅ መቀበያና አስተላላፊው ክፍሎች፣ ድምፅን ተቀብለው ወደ አእምሮ ያስፈላልፋሉ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እንደ ሕፃኑ ፍላጐት የመሳሪው ውጫዊ ክፍሎች ሊስተካከሉ ይችላሉ፡፡

ልጅዎ *የ'ኮክሊያ ኢምፕላንቱን'* በትክክል ሊጠቀምበት የሚያስችለውን ዘዴ ካላወቀ፣ ምንም ዓይነት ድምፅን ሊሰማ አይችልም፡፡ የኮክሊያ ኢምፕላንቱ በደንብ የሚሰራ ቢሆንም እንኳ፣ በ*'ኢምፕላንቱ'* በኩል መስማት በጤናማ ጆሮ ከመስማት የተለየ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ ድምጾቹ አሰልቺ ወይም ሲጥጥ… የሚሉ ናቸው፡፡ በግልፅ ከማይሰማ ከሬዲዮ ጣቢያ ጋር ያመሳስሉታል፡፡ የኮክሊያ ኢምፕላንት የተደረገላቸው ሕፃናት፣ የሚሰሙትን ድምፅ ለመረዳት ልምምድ ማድረግንና ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ ለመሆን ጊዜ መውሰድ አለባቸው፡፡ ሕፃናት በኮክሊያ ኢምፕላንት እንዴት መስማት እንደሚችሉ በክፍል ውስጥ ተቀምጠው ልክ እንደ አንድ ስልጠና በደንብ መሰልጠን ይኖርባቸዋል፡፡




ይህች ልጅ የቤተሰቦቿን ድምፅ መስማት ትችላለች፡፡ የእያንዳንዱን ሰው ድምፅና በሰዎች መካከል ያለውን የድምፅ ልዩነትት መማር ያስፈልጋታል፡፡

ከቀዶ ጥገናው፣ ከመሳሪያው፣ እና ከስልጠናው የሚገኙት ውጤቶች ለእያንዳንዱ ሕፃን የተለያዩ ናቸው፡፡ የኮክሊያ ኢምፕላንት ያላቸው፣ እና በስልጠናው በጣም ጠንክረው የሚሰሩ ብዙዎቹ ሕፃናት ድምጾችን ሊሰሙና ሊረዱ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶቹ የኮክሊያ ኢምላፕንት የተደረገላቸው ሕፃናት ንግግርም ለመማር ይችላሉ፡፡ ሌሎቹ ሕፃናት ደግሞ ድምጾችን ለመስማትና መናገር ለመቻል ይማራሉ፣ ሆኖም ግን በደንብ ውጤታማ አይሆኑም፡፡

## የ'ኮክሊያ ኢምፕላንት' ለቤተሰብዎ ጥሩ ምርጫ ነውን?

የኮክሊያ ኢምፕላንትን ለልጅዎ ጥሩ አማራጭ ሊሆን ይችላል ብለው ለመወሰን እያሰቡ ከሆነ፣ የሚከተሉትን ነገሮች ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ።

*የኮክሊያ ኢምፕላንትና የባለሙያ ድጋፍ በአካባቢዎ ማግኘት ይችላሉ?*
ብዙዎቹ ማህበረሰቦች በኮክሊያ ኢምፕላንት ዙሪያ ሊሰሩ የሚችሉ ሐኪሞችና የሰለጠኑ ባለሞያዎች የሏቸውም። አብዛኞቹ አገሮች ቀዶ ጥገናውን ማድረግ የሚችሉ አንዳንድ ሐኪሞች አሏቸው፣ ነገር ግን ሐኪሞቹ የሚገኙት በትላልቅ ከተሞች በሚገኙ ሆስፒታሎች ውስጥ ሲሆን የኮክሊያ ኢምፕላንት ማዕከልም ሊኖራቸው ይችላል።

የኮክሊያ ኢምፕላንት ማዕከል በአቅራቢያዎ ቢኖር በጣም ጠቃሚ ነው። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ማዕከሉን እርስዎና ልጅዎ ብዙ ጊዜ ለብዙ ዓመታት ይጐበኙት ነበር።

> የኮክሊያ ኢምፕላንት በአገራችን በኢትዮጵያ መኖር አለመኖሩን የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን ወይም መስማት የተሳናቸው ት/ቤቶችን በመጠየቅ መረዳት ይችላሉ። ሆኖም እስካሁን ካለን መረጃ አንፃር አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ገና አልተጀመረም።

*የቀዶ ጥገናው እና የኮክሊያ ኢምፕላንቱ (መሳሪያው) ዋጋ*
ቀዶ ጥገናው፣ መሳሪያው፣ እና በባለሙያዎች የሚሰጠው የዓመታት ስልጠና በጣም ውድ ነው። በህንድ አገር የኮክሊያ ኢምፕላንት አስር ሺ የአሜሪካን ዶላር ($10,000) አካባቢ ያስከፍላል። የመስሚያ መርጃ መሳሪያው ደግሞ 75 ዶላር አካባቢ ይሆናል። ልክ እንደ መስሚያ መርጃ መሳሪያ ሁሉ፣ ሕፃናት የኮክሊያ ኢምፕላንቱን ውጫዊ ክፍል (ከጭንቅላት ውጪ የሚገኘውን) ሊሰብሩት ይችላሉ። እነዚህን ክፍሎችም ለመተካት በጣም ውድ ሊሆን ይችላል።

*በቻይና አገር፣ ቀዶ ጥገናው፣ መሳሪያው፣ እና ስልጠናው የአንድ መካከለኛ ደመወዝተኛን የ 20 ዓመት ደመወዝ ሊሆን ይችላል*





*በሜክሲኮ አገር የኮክሊያ ኢምፕላንት ዋጋ በዚያ አገር የሜዲካል ዶክተርን የ4 ዓመት ደመወዝ ይሆናል*



ጊዜ ያለፈባቸውና ርካሽ የሆኑ 'ኮክሊያ ኢምፕላንቶች' እንደ አዲሶቹ (ዋጋቸው ውድ እንደሆኑት) በደንብ አይሰሩም። ጥቂት አገሮች፣ የኮክሊያ ኢምፕላንትን በነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ያቀርባሉ።



የኮክሊያ ኢምፕላንቶች (እንደ ሌሎቹ ህክምናዎች ሁሉ) መክፈል ለሚችሉት ሀብታሞች ብቻ መሆን የለበትም። ለአንድ ሕፃን ከሁሉም በተሻለ የሚጠቅመው የኮክሊያ ኢምፕላንት ሆኖ ከተገኘ፣ ቀዶ ጥገናውና አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች ሁሉ የሚገኙባቸው መንገዶች ሊመቻቹ ያስፈልጋል።

> በአገራችን በኢትዮጵያም መንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ እና የግል ኢንቨስተሮች ለዓይን የቀዶ ጥገና ህክምና ትኩረት የሰጡትን ያህል ለጆሮ ህክምናም (ለኮክሊያ ኢምፕላንት) ትኩረት ሊሰጡት ይገባል።

## የኮክሊያ ኢምፕላንቶች እና በሽታ

አንዳንድ ጊዜ የኮክሊያ ኢምፕላንት የመስማት ችሎታን የበለጠ ሊጐዳ የሚችል ህመምን ሊያስከትል ይችላል። የኮክሊያ ኢምፕላንት ያላቸው ሕፃናት ጆሮአቸውን ሲያማቸው በፍጥነት ማሳከም አስፈላጊ ነው። እንደዚሁም ደግሞ በልጅነት ጊዜ በሚከሰቱ በሽታዎች መከላከያ የሚሆኑ ክትባቶችን ለእነዚህ ሕፃናት በወቅቱ መስጠት በጣም ያስፈልጋል።



የኮክሊያ ኢምፕላንት፣ መሳሪያውና፣ ቀዶ ጥገናው ማጅራት ገትር የሚባለውን ከባድ በሽታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወይም ከዓመታት በኋላ ሊያስከትሉ ይችላሉ። ማጅራት ገትር በጣም ከባድ የሆነ በአእምሮ ላይ የሚከሰት ህመም ነው። አብዛኛውን ጊዜ በበሽታው የሚጠቁ ሕፃናት፡–

- ዕድሜአቸው ከ 5 ዓመት በታች የሆኑት ናቸው
- መስማት የተሳናቸው ይሆናሉ
- የጆሮ ህመም ያጋጥማቸዋል
- አብዛኛውን ጊዜ ይታመማሉ

ስለ ማጅራት ገትር በሽታ የበለጠ ለመረዳት በገፅ 205 እንዲሁም በሄስፔሪያን ፋውንዴሽን የታተመውን 'Where There Is No Doctor' የሚለውን መፅሐፍ ያንብቡ።

## ከቀዶ ጥገና በኋላ የሚደረግ እንክብካቤና ድጋፍ




የኮክሊያ ኢምፕላንት ለተደረገላቸው ታዳጊ ሕፃናት የቤተሰቦቻቸውና የባለሙያዎች ተጨማሪ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ሕፃናቱ ከቀዶ ጥገናው ከዳኑ በኋላ፣ የሚሰሟቸውን ድምጾች እንዴት ማዳመጥና መረዳት እንደሚችሉ ለዓመታት በባለሙያዎች ሊሰለጥኑ ይገባል። ቤተሰቦችም ከልጃቸው ጋር እንዴት መግባባት እንዳለባቸው ስልጠና ያስፈልጋቸዋል።